
# <u>በሻዕቢያ መጠቃታችንን ለማስረሳት የተመለመሉ ነገረፈጂ ሎቢስቶች</u>


## ጌታቸው ረዳ (ኢትዮጵያን ሰማይ አዘጋጅ Ethiopian Semay)

**getachre@aol.com**


የሚከተለው ምሬት፤ ድምፅ እና አደራ ታስታውሳለችሁ? ያ ድምፅ የማን ነው?




<< ዛሬ ሻዕቢያ ምፅዋን ተቆጣጥሬአለሁ በማለት የዓለምን መገናኛ ብዙሃን እንደሚያጨናንቅ ጥርጥር የለውም። ይህ ደግሞ ለኢትዮጵያ ሀገሬና ሕዝቧ ትልቅ አደጋ ነው። በቀይ ባሕር በራችን በኩል ብዙዉን ጊዜ ወረራ ፈጽመውብን በተደጋጋሚ ያሳፈርናቸው ፊት ለፊት ያልቻሉን ምዕራባውያን፤ሀገሮችና ዓረቦች ዛሬ የሻዕቢያ ጊዜያዊ ድል ሰምተው ይፈነጥዛሉ። ምናልባትም የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድምበር የሆነውንና ለዘመናት በአባቶቻችን የደም ዋጋ

ፀንቶ የቆየውን የባሕር በራችንን መዘጋት እንዲሁም ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ ባሕር አይደለም በማለት በምድር ተወስነን እንድንቆይ ይደረግ ይሆናል።ይህም ደግሞ የሞት ሞት ነው።

ኢትዮጵያ ሀገሬ የጀግኖች መፍለቂያና ገናና ታሪክ ያለት ሀገር ናት፤ በመሆኑም ጀግናው ሕዝቧ የባሕር በሩ በሻዕቢያ ተይዞና የጠላቶቹ መፈንጫ ሆኖ አይኖርም። የፈለገ ጊዜ ይቆይ እንጂ ሻዕቢያ ምፅዋን እንደያዘ ለዘለዓለምአይኖርም። ጊዜውን ጠብቆ የኢትዮጵያ ጀግና ጠላቱን ደምስሶ ምፅዋን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚያስረክብ እምነቴ የፀና ነው!>> ብርጋዴር ጀኔራል ተሾመ ተሰማ

*(አይ ምፅዋ ከሚል መጽሐፍ የተወሰደ። ደራሲው የዓይን እና የጆሮ ምስክር የነበረ የጦርነቱ ተካፋይና ከጀኔራሉ ጋር በቀርበት የሰራ፤ ታደሰ ተሌ)*

አይ ምፅዋን ያነበባችሁ ወገኖቼ፤ የጦርነቱ አስከፊነትና ለሀገር አንድነትና ክብር የተከፈለው መራራ የሕይወት መስዋዕትነት ምንኛ እጅግ ውድ እና መቸውንም የማይረሳ ነው። የሰው ሬሳ ከውሻ እና ከድመት አብሮ የተቀላቀለበት ለጠላታችን ለሻዕቢያ ወግኖ በምፅዋ ጦርነትና የከሕደቱ የወንጀሉ ተካፋይ የነበረው “የህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ” ክሕደቱ እንደተጠናቀቀ ወዲያውኑ የሰበከን ስብከት “ሻዕቢያ ወዳጃችን” እንጂ “ሻዕቢያ ጠላታችን እንዳልሆነ” ለማሳመን ያልጣሩትና ያልፈነቀሉት ድንጋይ እንዳልነበረ የምታውቁት የትናንት ትውስታችን ነው።

ሰሞኑን ደግሞ “ሮዛ አባድር” (ንአምን ዘለቀ ነው ይላሉ አንዳንዶቹ) በሚል ስም የውሸት ስም ከሚጠቀሙት ማንነታቸው ላላማሳወቅ በፍርሃት ዓለም ተከልለው እየተደበቁ ከሚጽፉ “ሱሪያቸውን ጥለው ቀሚስ ያጠለቁ.....” (የሐረር ወርቅ ጋሻውን አባባል ልዋስ እና) የግንቦት 7 እና የኦነግ ደጋፊ የሆነ ይህ ግለሰብ፤ ካሁን በፊት የኢሕአፓውን መሪ ሃማ ቱማን ኦነግና ኦብነግ ኢትዮጵያዊነትን አጥብቀው ይጠላሉ ብሎ ስዊድን ራዲዮ ካለው ኢትዮጵያ ራዲዮ በቃለ መጠይቁ በመናገሩ

“Ato Iyasu also didn't have any shame to put such kind of statement in accusing OLF as enemy of Ethiopia”

በማለት ስለ ኦነግ ጥብቅና ቆሞ “ኦነግ የኢትዮጵያ ጠላት አይደለም” እያለ የዘላበደውን ሳይበቃው ዛሬ ደግሞ በዘሐበሻ እና በኢካዴፍ ድረገጾች ላይ “Is Eritrea Foe or Friend to Ethiopia?” በማለት በጻፈው ርዕስ ውስጥ ደግሞ ስለ ሻዕቢያ ጥብቅና በመቆም፤

1) “Ethiopians don't have enemy than the TPLF gangs.

ETHIOPIANSEMAY

2) Ethiopia and Eritrea /these two countries will live side by side...
3) Ethiopians are murdered not by Shabia bullet, but by the barbaric TPLF Agazi militia.”
4) “Ethiopia remained land locked not because of Eritreans.”

እያለ ሲዘባርቅ አንባብችሁት ይሆናል። እነዚህ አራት ነጥቦች እንደ ሮዛ አባድር የመሳሰሉ የግንቦት 7 እና በኦነግ ደጋፊዎች ዘንድ ጎልተው የሚነገሩ ከባድሜ ጦርነት ወዲህ ሻዕቢያ የፈጠራቸው የፖለቲካ ስራዎች ናቸው።

ከነዚህ ክፍሎች ውጭ “አምቼ” ተብለው በሚታወቁ ትግርኛ በሚናገሩ ኤርትራዊያኖች የሚናቁ አማርኛ ሲናገሩ አማራዎችን የሚመስሉ አማርኛን አጣርተው መናገር የሚችሉ የሻዕቢያ ደጋፊዎች እና ባለስልጣን ኤርትራውያኖች (እንደ ግርማይ አስመሮም እና ሃይለ መርቀሬዎስ.....) በመሳሰሉት ዘንድም ተደጋግመው የሚነገሩ ናቸው።


ከላይ “ድብቁ ሰውዬ” የሚባለው በ “ሮዛ አባድር” ስም የሚጽፈው የሻዕቢያ እና የኦነግ ሎቢስት የሆነ የግንቦት ሰባቱ ሰውዬ የጠቀሳቸው “አራቱን ነጥቦች” እራሱ የሻዕቢያው መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ በቃለ መጠይቁ በትግርኛ አስር ጊዜ የሚደጋግማቸው ፕሮፓጋንዳዎች ናቸው። ሻዕቢያ እነዚህ ነጥቦች በኢትዮጵያዉያን ሕሊና ተቀባይነት አግኝተው በኢትዮጵያ ሚዲያዎች ሽፋን አግኝተው እንዲነገሩ የሚፈልገው ለምንድ ነው ?

በነጥብ አንድ የሰፈረው

“ኢትዮጵያዊያን ያለ ወያኔ ሌላ ጠላት የላቸውም” የሚለው ነጥብ ስትመለከቱ፤ እራሱ ኢሳያስ ይህችን ቃል ሲደጋግማት የምትሰሙትበት ምክንያት፤ ሻዕቢያ በኢትዮጵያዉያን ዜጎች እና በኢትዮጵያ ሉአላዊነት ላይ ከፍተኛ ወንጀል መፈጸሙን እና አሁንም እየፈጸመ እንደሆነ እና ያንን ለመሸፋፋን እንዲመቸው የሕዝባችነን ቀልብ/አትኩሮት አስቀይሮ ወያኔን እንደ ብቸኛ ጠላት አድርጎ እንዲታይ፤ በጠላትነት እንዳይፈረጅ፤ከሰራው ወንጀል

ETHIOPIAN SEMAY

ነፃ ለመውጣት ካቀዳቸው ስልቶቹ አንደኛው ማጃጃያው/ዳይቨርዢነሪ ስልት ነው።




( ከላይ ላለው ፎቶ ካርቱን ለስዓሊው እና ለአሌፍ መጽሔት ምሳጋና አቀርባለሁ።ኮፒ ፔስት ኢትዮጵያን ሰማይ ብሎግ)

ይህ ሕሊናን የማስቀየር "ሳብቨርሲቭ/ሴራ" ደግሞ አባዝተው አሳምረው ለሕዝባችን የሚያዳርሱለት ወኪሎች/ሎቢስቶች ይፈልጋል። ካሁን በፊት በኦነጎች በኩል አሰራጭቶታል፤ ዛሬ ደግሞ እነኚህ የግንቦት 7 አዲስ የሻዕቢያ ተቀጣሪ ወንድሞች እና እህቶቻቻን ይህንኑ ሻዕቢያ አጥብቆ የሚሰራበትን "ወያኔ ብቻ እንጂ ሻዕቢያ ጠላታችን አይደለም" የሚለው ፕሮፓጋንዳ እንዲሰብኩለት ሻዕቢያ ለብዙ አመታት የሰራበት "ስትራተጂ" ተቀብለው ሲያስተጋቡለት **የሳብቨርሲቩ ዘመቻ** የአጠባው ስልት ግቡ እየመታለት መሆኑን ከእነዚህ ቡድኖች ልሳን ማረጋገጥ ትችላላችሁ።

ሻዕቢያ ጠላት አይደለም፤ ብለው የግንቦት 7 መሪዎችና ደጋፊዎቻቸው እየተጋጩ ያሉት በቀጥታ ሕይወታቸው ለአገራቸው የገበሩ *"ጊዜውን ጠብቆ የኢትዮጵያ ጀግና ጠላቱን ደምስሶ ምፅዋን ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚያስረክብ እምነቴ የፀና ነው።"* ብለው ሻዕቢያን

በጠላትነት ፈርጀው ለህይወታቸው ሕልፈተ-ምክንያት የሆነው ሻዕቢያ፤ "ጠላት" ነውና ጊዜን ጠብቃችሁ "ደምስሱት" ብለው ከነገሩን ከአርበኛችን ከጀኔራል ተሾመ ተሰማ እና በሚሊዮን የሚቆጠሩ አርበኞቻችን ጋር ቅራኔ መግባታቸው አገር ውስጥም ሆነ እውጭ አገር የሚኖር አገሩን የሚወድ የኢትዮጵያ ሕዝብ እንድያውቀው ካሁኑኑ እናስገነዝባለን።

<u>ወደ ሁለተኛው ኤርትራን እንደ አገር የመቀበሉ ነጥብ፤-</u>

ሌላው ትግርኛ ለምናነብ ዜጎች ሻዕቢያ የሚጽፉቸው እና በዘፈን እና በግጥሙ ምን እያለ እንደሚያስተላልፍ ስለምናዳምጠው እራሳቸውን ለሽያጭ ያመቻቹ ኤርትራን **"አገር"** እያሉ እንደ ሕጋዊ አገር የሚጠሩዋት እነኚህ ቀላዋጭ ግለሰቦች የኮለኔል ጐሹ ወልዴን አባባል እዚህ ልዋስና "የኢትዮጵያ ሕዝብ ያገለለ፤ የኤርትራው "**ሓባሽ** "እና የትግሬው "ኪም ኤል ሩዥ/ ኮለኔሉ **"ኪም ኤል ኑዋር"** ይሏቸዋል" የፈጠሩዋትን "የስቃይ፤የጣዕረ ሞትና የኡኡታ "**አገር**" የኤርትራ አዳዲስ ሎቢስቶች ሆነው ምፅዋ ላይ የወደቁብንን የጀግኖቻችንን አደራ እንዳይደመጥ በየሚዲያው "ከሻዕቢያ በላይ ሻዕቢያ" በመሆን የወያኔንን አሳፋሪ ቅጥረኛነት እንደገና በመድገም የምፅዋን ጀግኖቻችን ያስተላለፉልንን የአደራ ቃል ሲያረክሱት ይገኛሉ።

እኛ አደራ አንበላም! በሻዕቢያ መጠቃታችንን አንረሳም! ኤርትራ የሚባል አገር አናውቅም፤ ኤርትራ የኢትየጵያ ክ/ሃገር ነች! ጣሊያን በ1928 ዓ.ም ሲወርረን ጥንቱንም ፈርሶ የነበረው የውጫሌው ውል በ1928 ሲወርርን "ዉሉ ፈርሷል"! ስለዚህ በቃሉ መሰረት ጣሊያን ሲለቅ "ኤርትራ" ብሎ የሰመው "ባሕረ ምድር" ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ እንደሚመልስ ፈርሞ የገባውን ቃል ኪዳን የጸና ይሆናል። በ1928 አገራችን ሲወር፤ አዲስ መልክአምደር/ካርታ አዘጋጅቶ ኤርትራን ከእናት ክፍሏ በሕጋዊ የወረራ ውህደት አዋህዷታል። ስለዚህም ጃንሆይም ሆኑ መንግሥቱ የተከተሉት አገርን የመከላከል ጦርነት ሕጋዊና ተቀባይነት ያለው የሉአላዊነት ጦርነት ነው። ጭካኔ ነበረበት? አዎ! ጭካኔ ያልሰራ ማን አለ? ሻዕቢያም ወያኔም ከደርግ በባሰ መልኩ በሰው ልጅ ፍጡር ጭካኔ ፈጽመዋል። ስለዚህ ስለ ኤርትራ ጥብቅና የቆማችሁ ተመጻዳቂዎች ሆይ አፋችሁን ዝጉ!

ሴረኛው ግብፃዊው "ቡጥሮስ ጋሊና" አሜሪካዊው "ሄርመን ኮሆን" ወይንም "ኤርትራዊው ሓባሽ" ወይንም "ማሌሊታዊው የትግሬው ኪም ኤል ኑዋር" የጠነሰሱትን ኤርትራን እንደ "ሀገር" የማወቁን አዚም ከቶ እስከ መጨረሻ ሞታችን ድረስ አንቀበለውም። ምክንያቱም ሕዝባችን የባለቤትነትን የይገባኛል ጥያቄው ታፍኖ እስካሁን ስላለ፤ ያልተወራረደ ያልተጠናቀቀ ሂሳብ አለን እና እስኪወራረድ ድረስ "ኤርትራ እንደ አገር አንቀበልም!! ምላሳችሁን ሰብስቡ!!!!"

ለምን? ምክንያቱም ፤ ትግሬ ተመስሎ ትግሬዎችን አሳጅቦ የራሱ ሰላዮችን (ሙሴ እና የማነ ጃማይካን) አስልኮ ድርጅቱን መስርቶ፤ በተንኮል እና በጠመንጃ ጠባቂዎቿ ባለቁባት ሰዓት ኢትዮጵያን አስገድደው በድንገት፤በደፈጣ፤በተንኮል ክብረ ድንግልናዋ ሬፕ

ETHIOPIAN SEMAY

አድረገዋታል! ታምጻለች! ። መሬት ላይ ጥለው አንደረጋገጧት ሁሉ፤ ወረበላዎቹ አማጺዎቿም በተራቸው ሲደክሙ ተምበርክከው ያልተወራረደውን ሂሳብ እስኪያወራርዱ ድረስ ከአማጺዎቿ ጋር ፀብ እንጂ ወዳጅነት የለንም!

ግንቦት 7 ከወረበላዎች እና ዓለም ካወገዛቸው "የኤርትራ ኮንትሮባንዲስቶች፤ማፊያ ነብሰ ገዳዮች" ጋር ወዳጅነተ አበጅተው ሀገራችን ጠላፊዎቿን እንድትረሳ እያደረጉ ያሉትን አሳፋሪ የቅጥረኛነት ተግባር ሕዝባችን በነቂስ ማውገዝ አለበት።

፤ይልቁንም በጣም የሚገርመው ደግሞ ሻዕቢያ ዛሬም ቢሆን በ1983 ዓ.ም ግባቸው ያልተሳካላቸው ጊዜ እየጠበቁ ያሉ ተገንጣዮችና የአማራን ሕብረተሰብ በዘር ጽዳት ዘመቻ የጨፈጨፉ ወንጀለኞች ኤርትራ መሬት ላይ መሽገው አስፈለጊው ስልጠና እና አንክብካቤ እየተደረገላቸው ዓይናችን እያየን ባለበት ሰዓት ነው 'ሻዕቢያ ወዳጃችን ነው" እያሉ እየሰበኩን የሚገኙት።

ቁስላችን ተሽከመን ዝም ማለታችን ሳይበቃን፤ በቁስላችን ላይ እንጨት እየሰደዱ ይነካኩናል። የግንቦት ባንዳዎች ግልጽ እንዲሆንላቸው የምንሻው በባርነት ቅንበር ተይዘው ሳሕል በረሃ ላይ ያሉት ወገኖቻችን ሁኔታ እስካላወቅን ድረስ ከዚህ ጠላትም ሆነ ከዛኛው ጠላት መሬት ቢገለበጥ የምንወዳጅነት ምንም ታአምር የለም።ይህ ደግሞ መጪው ትውልድ የእኛን ብዕር እና ቅስቀሳ አድምጦ ጠላፊዎቿን በተራቸው ያንበረከካቸዋል። የጄነራሉ ትንቢትም የነገረን ይህንኑ ነው። ይደረጋል። ባንዳዎች አትጠራጠሩ!

ባሕራችን ተዘግቶ መኖር "የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ድምበር የሆነውንና ለዘመናት በአባቶቻችን የደም ዋጋ ፀንቶ የቆየውን የባሕር በራችንን መዘጋት እንዲሁም ቀይ ባሕር የኢትዮጵያ ባሕር አይደለም በማለት በምድር ተወስነን እንድንቆይ መደረጉ የሞት ሞት ነው።" ብለው ጀግኖቻችን እነ ጄኔራል ተሾመ ነግረውናል እና የጀግኖቻችንን አደራ ከቶ አንባላም! የልጁን ሥጋ እና አደራ የምትበላ "ድመት ብቻ ነች"። እኛ የምናስብ ሰዎች እንጂ ለሆዳችን የምናድር የምድር አራዊቶች አይደለንም"። ባንዳዎች ይህንን እንድታወቁልን እንፈልጋለን! እኔ ጌታቸው ረዳ ድሮ አገሬ ገብቼ ከባንዳዎች ጋር እየተሞዳሞድኩ 'ታጁር" እሆን ነበር። ግን አደራ አለብኝ፡ እዚሁ እሞታታለሁ እንጂ መጻሕፈቶቼ ለትውለድ ትቼ ውግያው አስተላልፌ ቀኔ እስኪደርስ እና እስክሰናበት ድረስ ከናንተው መሳይ ባንዳዎችና እናንተን የቀጠሩ አለቆቻችሁ ባንዳዎች ጋር ምንም ድርድርና ዕርቅ የለም! ውርደት በቃን! ስንት ጊዜ እንሞኝ?!!!!!

አንባቢዎቼ እና የቅርብ ወዳጆቼ ሆይ!

ጥቃታችንን ለማስረሳት የተመለመሉ እነኚህ አዳዲስ የሻዕቢያ ሎቢስት ነገረ ፈጂዎች፤ የረሱት ነገር አለ። እኛ ተጠቅተናል። እነዚህ ሰዎች አልተጠቁም ይሆናል። ወይንም ጥቃትን የመርሳት አዚም በኢትዮጵያዊያን ዘንድ የዘመናችን "ወረርሺኝ" እየሆነ መምጣቱ የሳብቨርሲቮቹ እና

ETHIOPIANSEMAY

የዳይቨርጢዢነሮቹ/ የሴረኞቹ እና የአቅጣጫ አሳሳቾቹ መርሃ ግብር ግቡን በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ መሆኑን ምልክት ነው ። የዚህ ጥቃትን ተሎ የመርሳት አስገራሚ ክስተት ፤ ዕድገትና ክንዋኔ ሳስብ ፤ አንድ ስሙን በረሳሁት ኢትዮጵያዊ መጽሔት **"ጥቃትን በመርሳት ሽልማት የሚሰጥ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያዊያን ሽልማቱን ይወስዱት ነበር"** ብሎ ነበር። እርግጥ ይህ መሬት ያልነካ ትክክለኛ አባባል ነው። እኛ ተዋርደን ገራፊዎቻችን እና አዋራጂዎቻችንን በማግሰቱ ስንክባቸው የምንታይ ሕብረተሰብ እየሆንን የመምጣታችን ሁኔታ እጅግ እያሳሰበኝ መጥቷል። እነ ኑዋይ ደበበ እምባ እያቀረሩ፤አዲስ አበባ ስታዲዮም ውስጥ

አንደኛው ሲክብሽ አንዱ ያፈርስሻል

አንዱ ሲያመርትልሽ ሌላው ይዘርፍሻል

አንዱ ሲሞትልሽ ሌላው ሲሾምብሽ

ምነድነው ነገሩ ዘር ያልበቀለብሽ?

አንቺ እናት አገሬ አረ ማን ያስብሽ?......"

እያለ ሲያዜም "አገሬ ሰው አጣሽ ወይ! እየቆዘመ አምባውን ሲያወርድ ቆይቶ ተመልሶ "አፈረሱሽ" "አጠቁሽ" ሲላቸው ከነበሩት በንቅዘት/በሙስና የቀረቀዙ ዘረኞች እና አፍራሽ ሃይሎች ጋር ሆኖ ጥቃቱን ተሎ ዘንግቶት ለአጥቂዎች የሙገሳ ዜማ እያዜመ ማየት "በዳይመንሺያ" በሽታ የምንሰቃይ ጥቃትን ተሎ የምንረሳ "ረሺዎች" መሆናችንን እጅግ አዝናለሁ።

ቂም መያዝ ተገቢ እንኳን ባይሆንም 'ጥቃታችን" ገና ሳይበርድ፤ ከጥቃት ወደ ጥቃት ተደራራቢ ጥቃት እየፈጸመብን፤ "ተገንጣይ ቡድኖችን" እያሰለጠነ እያባዛ አገራችንና የሕዝባችንን የወደፊት ሕልውና እንዲናጋ ዛሬም እየሰራ ባለበት ሁኔታ፤ ከሻዕቢያ ጎን ቆመው ለሻዕቢያ ጥብቅና እየጻፉ "ጠላታችን" አይደለም፡ እያሉ ሲሰብኩን "የወያኔን ቅጥረኛ ታሪክ አንደገና የሚደግም ተቃዋሚ አይኖርም ይሆናል ስል የነበረውን ዛሬ ተደግሞ ስመለከት የሀገሬ መጻኢ ሕልውና እጅግ ጥያቄ ላይ ገብቷል።

<u>ወደ 3ኘው ነጥብ ልሂድ፡-</u>

ኢትዮጵያዊያን የሚገደሉት የሚታፈኑት የሚሰቃዩት በወያኔ ጥይት እንጂ በሻዕቢያ አይደለም በማለት እየነገረን ያለው በሦስተኛው ረድፍ ያነሳው ነጥብ ስንመለከት፡ ይህ ግለሰብ ፍጹም ጸረ የትግራይ ሕዝብ ነው፤ ወይንም የሻዕያ ተፈጥሮአዊ ባሕሪ ፈጽሞ አያውቀውም ማለት ነው። ሻዕቢያ በኤርትራ አዋሳኝ ያሉት የትግራይ አዋሳኝ ዙርያ መለሽ ድምበሮች በሙሉ እስከ ዛሬ ድረስ ሰዎች እየታፈኑ፤ ከብቶቻቸው እየተዘረፉ፤ ማር ንባቸው ተጎርጉሮ ተዘርፎ ብቻ ሳይሆን ንብ አንዳይሰፍርበት ዛፎችን እንዳለ እያቃጠለ

ETHIOPIAN SEMAY

እና እየቆረጠ የትግራይን ሕዝብ በተለይ የኢሮብን ሕዘብን እና በየግል ተነሳሽነት ወርቅ አለበት በሚባለው የትግራይ ድምበሮች ለወርቅ አደና የተሰማሩ የቀን እንጀራቸውን ለመፈለግ ሲሄዱ ታፍነው የተወሰዱ ትግሬዎች ዛሬም በሻዕቢያ እየተሰቃዩ ናቸው፡ የት እንዳደረሳቸውም የሚያውቅ የለም። እርግጥ አንዳንዶቹ ከወደ መጨረሻ ጽሑፌ በአውድዮ ማስረጃ ከአንድ የድርጅቱ ተዋጊ የነበረ በግድ ወደ ድርጅቱ የተመለመለ ከኢትዮጵያ የተባረረ ኤርትራዊ እንደነገረን እየታፈኑ የሚሄዱ የድምበር አካባቢ የትግራይ ኗሪዎች "ድምሕት" እያለ እራሱን የሰየመ 1/3 ኛው (እሩብ) በኤርትራኖች የተሞላ የሻዕቢያ ቅጥረኛ የሽምቅ ተዋጊ እንዲቀላቀሉ እንደሚደረግ እናውቃለን።

አስገደ ገብረስላሴ በቅርቡ በጻፈው መጽሀፉ ላይ እንዲህ ይላል

"በሰሜኑ (ትግራይ) አገራችን የሚኖሩ ዜጎቻችን ከሚኖሩባቸው ገጠሮች ደንቅ ደፈጣ እየተደረገባቸው እየታፈሱ በሺዎቹ የሚቆጠሩ  በሻዕቢያ ታፍሰው በሳሕል በረሃዎች በ15ኛው ክፍለዘመን  የሰው ፍጡር "ጊላ/ባርያ" እየተባለ ግፍ ሲፈጸምበት አንደነበረው ዓይነት አያያዝ የተያዙ ዜጎቻችን አሉ።" ይላል አስገደ።

ሮዛ አባድር የትግራይ ሕዝብ ኢትዮጵያ አካል አይደለም፤ ወይንም የትግራይ መሬትም ሆነ እዛው ሚኖር ፍጡር ኢትዮጵያዊነ አይደለም እና አያገባኝም ካላለ በስተቀር፤ ሻዕቢያ እስከ እዚችው ደቂቃ ድረስ በትግራይ ሕዝብ ላይ ያላባራ ጥቃት እየፈጸመ መሆኑን ሊያውቀው በተገባው ነበር። ስለዚህ ወያኔ እንጂ ሻዕቢያ የኢትዮጵያን ሕዝብ እየገደለ እያፈነ፤ እየገረፈ፤እያሰቃየ አይደለም፤ ብሎ ሲል የትግራይ ሕዝብ በሻዕቢያ ጥይት ሲገደል ምኑም አይደለም ማለት ነው። ለዚህም እንዲህ ያለ ግድ የለሽነትና ለትግራይ ኗሪ ቀን ሙያተኛ እና ድሃ ገበሬ ሻዕቢያ እያፈነ ሲያሰቃየው ደንታ-ቢስ መሆን  የቅጥረኛነት ጉልህ ማስረጃ ነው።

<u>ወደ 4ኛው ነጥብ እንሂድ፤-</u>

ለመሆኑ አራተኛው ነጥብ ደግሞ ኢትዮጵያ የባሕር በርዋን ያጣችበት ምክንያት በወያኔ እና በመንግሥቱ/በሃለስላሴ እንጂ "በሻዕቢያ" አይደለም ብሎ ለዳር ድምበራችን የተዋደቁት እና የተሟገቱትን ወገኖቻችንን ሲወነጅል፤ ሮዛ አባድርም ሆነ የግንቦት ደጋፊዎች "ወያኔ እና ሻዕቢያ" ምን እና ምን መሆናቸው አልገባቸውም ማለት ነው። አዲስ አበባ መንበረ መንግሥቱን ተቆጣጥሮ ሥልጣን ላይ ያለው ቡድን ማን ነው? ኤርትራዊያን ሻዕቢያዎች ናቸው!  ጥቂት የትግራይ ተወላጆች ካሉባቸውም 'አንደ ግንቦት 7 ቶቹ" ከሻዕቢያ በላይ ሻዕቢያ" ለመሆን የሚጥሩ ከሃዲ ቅጥረኞች ናቸው። የሁለቱም ድምር ጥንቅሮች የሚያስገኙን  የባሕሪ ማጠቃለያው የማን ተከለ ሰውነትን ያሳየናል? የሁለቱም ድምር ውጤት የሚያሳየን፤ እኔ እና የኢትዮ ሚዲያ አዘጋጅ አብርሃ በላይ ሁሌም እንደምንለው "ኢትዮጵያን እየገዟት ያሉት ቡድኖች ሻዕቢያዎች ናቸው" ብለን ብዙ ጊዜ ተናግረናል። የግንቦት 7 አባሎችና መሪዎች አነ "ሮዛ አባድር" ይህንን አያውቁትም።

ለያውቁትም ፍላጎትና ጥረት አያደርጉም። ምክንያቱም አንዴ በቅጥረኛ ሎቢስት ሥራ ከተሰማራህ ሌላ ተልዕኮ መፈጸም አትችልም።

ወየኔ ማን ነው የሚመራው? መሪያቸው መለስ ዜናዊም ሆነ ስብሓት ነጋ፤ ሥዩም መስፍን… ወዘተ. ወዘተ…..ወዘተ. ካንደበታቸውም ሆነ ከስራ አፈጻጻማቸው ኢትዮጵያዊያን ወይስ ሻዕቢያዊያን? እኔ እየጠየቅኩዋችሁ ነኝ ( I am just challenging you!) ፤ መልስ ስጡኝ እንጂ!? እነዚህ ናቸው እነ ሮዛ አባድርም ሆኑ እነ ብርሃኑ ነጋ እና ጀሌዎቹ “ወያኔ እንጂ ሻዕቢያ ጠላት አይደለም” እያሉ የሚሉን። እነ መለስ ዜናዊ እነ ሥዩም እና ስብሓት የወያኔ መሪዎች ናቸው፤ እነዚህ ግለሰቦች ደግሞ ከኢሳያስ በላይ ለኤርትራዊያን የሞቱ የደሙ፤ የቆሰሉ፤ሳይሸሽጉን ለእነ ጀኔራል ተሾመ ተሰማን ህየውት የቀዘፉ፤ ስለ ኤርትራ መሞት ፤መቁሰል፤ ክብር እና ጀግንንት መሆኑን ዛሬም ለኤርትራ ለመቁሰልም ሆነ ለመሰዋትነቱ፤ ዝግጁነታቸውን በይፋ ያስታወቁን ሰዎች ናቸው። ታዲያ እንዴት ወያኔዎች ማለት ሻዕቢያዎች አይደሉም ተብሎ ደንቁርና ይሰበካል? “ኢትዮጵያ ሲመሰከርባት እንጂ ሲመሰከርላት አላየንም” የሚለው የዜጎች እሮሮ ዛሬም በአዳዲስ ቅጠረኞች በኩል ሻዕቢያ ሳይሆን ወደቡን የዘጉት ወያኔዎች ናቸው በማለት ሲከራከሩ ‘ወያኔዎችና ሻዕቢያ’ መንትያዎች መሆናቸውና ስለ ኤርትራ ጥብቅና የቆሙ የባሕር ወደቦቻችንን ያስነጠቁን የኢትዮጵያ ካባ የለበሱ፤“ሻዕቢያዎች” ናቸው።

ቲ ፒ ዲ ኤም እያለ እራሱን የሚጠራ ሌላው ከትግራይ የበቀለ ባንዳ ደግሞ በሻዕቢያ ተዋጊ ሃይሎች በብዛት የተገነባ እና ለሞት ቅጣት የተበየነባቸው ኤርትራኖች ካሉም ወደ ቲፒዲኤም እየተላኩ እንዲረሸኑ የርሸና ስራ የሚያከናውን ቅጥረኛ ድርጅት ስለ መሆኑ ይህንን ማስረጃ እና ቃለ መጠይቅ በትግርኛ አድምጡ። ትርጉሙ ያልገባችሁ ካላችሁ ጊዜ ስጡኝ እና እተረጉምላችኋለሁ። እነሆ በግድ ወደ ቲፒዲኤም ተመልምሎ የነበረ ብዙ ወንጀል የተመለከተ፤ የሃይል መሪ ሆኖ ሁለት አመት ያገለገለ፤ ኋላ ሸሽቶ አምልጦ ወደ እውጭ አገር ከመጣ ሁለት አመት የሆነው ከኤርትራዊው አንደበት ከባለቤቱ አፍ አድምጡት እነሆ፡-

Eritrea: ኣባል ደምሒት ዝነበረ ኤርትርራዊ 20130301 Eritrea: ኣባል ደምሒት ዝነበረ ኤርትርራዊ 20130301

https://youtu.be/HK7r4qdmzbM

አመሰግናለሁ ጌታቸው ረዳ **getachre@aol.com**

ETHIOPIAN SEMAY